የኢትዮጵያውያን ማህበር በስዊዘርላንድ

ASSOCIATION DES ETHIOPIENS EN SUISSE

ኢ.ማስ.AES

Rue H. F. Amiel 20 ; 1203 Genève
emas.aes@gmail.com

# እውነት ትዘገያለች እንጂ አትቀርም!

ውድ የኢትዮጵያ ማህበር አባላቶች እንዲሁም በማህበሩ አላማ ላይ ተመርኩዛችሁ ማህበሩን አቅማችሁ በፈቀደ በቅርብም በሩቅም የተቻላችሁን ሁሉ የሞራልም ሆነ የገንዘብ እርዳታ ላደረጋችሁ ሁሉ ፤

ማህበሩ ነጻነቱን እና ህጋዊ መብቱን ለማስከበር በፍርድ ቤት እንዲቆም በተገደደበት ጊዜ የመረጣችሁት ኮሚቴ ላይ ከፍተኛ እምነት ጥላችሁ አብራችሁ ለአለፉት አመታት ከጎኑ በጽናት ለቆማችሁ ሁሉ፤

እንኳዋን ደስ አላችሁ!

የኢትዮጵያውያን ማሕበር በስዊዘርላንድ (ኢ.ማስ)ን የማፍረስ ተልኮ ተቀብለው ሲንቀሳቀሱ የነበሩት ወገኖች በፍርድ ቤት ተሸንፈዋል። የማህበሩ አባላት ድምጽ እንዲከበር ፍርድ ቤቱ ብይኑን ሰጥቶአል ። የምንኖርበት ሃገር ስዊዘርላንድ የህግ ልዕልና ያለበት ሃገር በመሆኑ ወያኔ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚያደርገው የሕዝብን ድምጽ ረግጦ በጉልበት እራስን በሕዝብ ላይ መሾም ወይም ማሕበሩን በጉልበት ተቆጣጥሮ የወያኔ አገልጋይ ማድረግ አይቻልም።

ኢ.ማስ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በስዊዘርላንድ ለሚገኙ ኢትዮጵያዉያን የስደት መብት መከበር ከሚያደርገው ትግል ጎን ለጎን በተለያየ ወቅት በችግር ላይ ወድቀው የነበሩ ወንድሞችና እህቶችን አቅም በፈቀደ ሲረዳ ቆይቶአል። ከዚህም በተጨማሪ በሃገር ቤት ለሚኖረው ሕዝባችን ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብት መከበር ፤ ለፍትህ በሃገራችን መስፈን ፤ ለአምባገነናዊና አረመኔያዊ አገዛዝ መወገድ በስዊዘርላንድ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የድርሻቸውን እንዲወጡ ስብሰባዎችን እና ሰላማዊ ሰልፎችን ከማዘጋጀት በተጨማሪ ከተለያዩ መንግስታት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች ዘንድ በመገኘት የሕዝባችንን ብሶት አሰምቶአል ፤ በሕዝባችን ላይ የሚፈጸመውን ግፍ እና በደል አጋልጦአል ።

ይህ ለሃገር እና ለሕዝብ ያለው ተቆርቋሪነት ነው ኢ.ማስን በወያኔ ጥርስ ውስጥ ያስገባው። ይህን ሕዝባዊ ተልዕኮውን ለማደናቀፍ እና ከተቻለም ለማስቆም ነው በኤምባሲው ስውር አስተባባሪነት በጥቅም በተገዙ ተላላኪዎቹ የማደናገር ፤ የማሸመድመድ እና የመበተን ዘመቻ የተከፈተበት።

ይህ ዘመቻ እንደታሰበው ኢ.ማስን ማፍረስ ባይቻለውም በተለያዩ ወቅቶች የህግ ማደናገሪያዎችን እና አሉባልታዎችን በመጠቀም ሕዝባዊ ትግሉን በስዊስ አላዳከመውም ማለት አይቻልም።

ኢ.ማስን የማፍረሱ ተልዕኮ በኢ.ማስ አባላትና ደጋፊዎች ቆራጥ ትግል ከሽፎ በፍርድ ቤት ውሳኔ ዕልባት ቢያገኝም የማሕበሩን ሕጋዊ ሕልውና ማፈን የተሳነው ወያኔ በቅርቡ ደጋፊዎቹን በኤምባሲው ሰብስቦ ተለጣፊ ማሕበር እንዲያቋቁሙ አመራር ሰጥቶአል። ዛሬም እንደትላንቱ ይሕን ዕኩይ ተግባር ለማስፈጸም የተቃዋሚ ጭምብል የለበሱ ተላላኪዎቹን በኢትዮጵያውያን መሃል አሰማርቶአል። በስዊስ የሚኖሩ ሃገራቸውን እና ሕዝባቸውን የሚወዱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከኢ.ማስ ጎን ቆመው ወያኔን እና ተላላኪዎቹን እንዲታገሉ ኢ.ማስ ጥሪውን ያቀርባል።

ወያኔ ያለውን አቅም ሁሉ ተጠቅሞ ቢዘምትበትም ኢማስ በፍርድ ያገኘውን ነጻነት ተጥቅሞ የተመሰረተበትን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ በቆራጥነት ትግሉን ይቀጥላል። በስዊዘርላንድ የሚኖሩ ኢትዮጰያዊያን ደስታና ችግራቸውን በጋራ የሚካፈሉበት አሰባሳቢ መድረክ መሆኑን እና እንዲሁም የሕዝባችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት እንዲከበር ኢትዮጵያዊያን እንደ ዜጋ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉና ድምጻቸውን እንዲያሰሙ ማስተባበሩን ከበፊቱ በበለጠ አጠናክሮ ይቀጥላል። ኢማስ የቆመላቸውን እነዚህን አብይ አላማዎች በአግባቡ ተግባራዊ እንዳያደርግ ማስቆም ከቶውኑ እንዳማይቻል በአለፉት አመታት ባካሄደው እልህ አስጨራሽ ትግል በተግባር አስመስክሮአል።

ኢማስ የማህበሩን አሰራና እና አካሄድ ለማጠናከርና ከአባላቱና ከደጋፊዎቹ ጋር ሰፊ ውይይት ለማካሄድ በቅርቡ ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል። በዚህ ጉባኤ ላይም ያለፉትን ጥቃቅን አለመግባባቶችና ስህተቶችን ይቅር ተባብለን በአርቆ አስተዋይነት ይበልጥ አቀራርበውና አስተባበረው ሊመሩን የሚችሉ አባላት ያሉት አዲስ የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ እንዲመረጥ በቂ ዝግጅት ይደረጋል።

ኢማስ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ቤት እንደመሆኑ ኢትዮጵያውያን ያላቸው የአመለካከት እና የሃሳብ ልዩነት እንደተጠበቀ የህዝባችንን ጭንቀትና መከራ በጋራ ለማዳመጥ እና ብሶቱን በጋራ ለመታደግ አብረው መስራት ይቻላቸዋል ብሎ ያምናል። ከዚህ ዕምነት በመነሳትም ኢማስ ዛሬም እንደትላንቱ በስዊዘርላንድም ሆነ በመላው ዓለም ከሚገኙ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሃገርን እና ሕዝብን አስቀድመው ከሚታገሉ ኢትዮጵያውያን ስብስቦች ጋር በመከባበር እና በመተባበር ለመሥራት ዝግጁነቱን ያረጋግጣል።

ኢማስ ኢትዮጵያዊነት የጋራ ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ እና ሃገራዊ ህልውናችን እንዲቀጥል የሚደረገው ትግል የሁሉም ጤነኛ እና በጎ አሳቢ ኢትዮጵያዊ ሃላፊነት ነው ብሎ ያምናል። ይህን የጋራ ሃላፊነት በጋራ ለመወጣት ያለን አንድና አንድ አማራጭ እድገትን አመንጭ በሆነ ልዩነት ላይ ተመስርተን ተባብረን እና ተከባብረን መስራት ስንችል ብቻ ነው።

ሃገራችን ኢትዮጵያ ከምንጊዜውም በላይ የልጆቹዋን ሕብረት የምትሻበት ወቅት ላይ እንደምትገኝ ሁሉም የተረዳው ሃቅ ነው። በመሆኑም ዛሬም እንደትላንቱ ጥቃቅን ልዩነቶችን እያራገቡ ኢትዮጵያውያንን ለመከፋፈል እና ለመበታተን የሚሩዋሩዋጡ የወያኔ ስውር ተላላኪዎች ሰለባ እንዳንሆን ተጠንቅቀን መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል።

ዛሬም እንደትላንቱ በጋራ ቆመን እርስ በርስ እንረዳዳ። ዛሬም እንደትላንቱ በጋራ ቆመን የሃገር እና የህዝብ ጠላቶችን እንታገል።

የፍርዱን የውሳኔ ሰነድ ከዚች አጭር መልእክት ጋራ አያይዘን ልከናል።
የፈረንሳየኛ ቋንቋ የካንቶን ቋንቋችሁ ላልሆነ የማህበር አባላቶቻችን ፍርዱን ለመተርጎም ዝግጁ ነን።

የኢትዮጵያውያን ማሕበር በስዊዘርላንድ (ኢማስ)